Sept 17,2013

አማርኛ መንፈሳዊ ጽሁፎች

# እግዚአብሄር ይናገራል

እግዚአብሄር በሶስት ዋና ዋና መንገዶች ሊናገረን እንደሚችል መዝ 19፡1-14 ላይ እናስተውላለን፡፡እነርሱም፦

## 1.በሚታየው አለም ባሉ ግዙፍና ድንቅ የእጁ ስራዎቹ ይናገረናል

ይህንን ሀሳብ በሚገባ የሚገልጽልን ቃል መዝ 19፡1-4 ላይ ያለው ቃል ሲሆን እንዲህ ይነበባል፡-
<<ሰማየት የእግዚአብሄርን ክብር ይናገራሉ፤የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል፡፡ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፤ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች፡፡ነገር የለም መናገርም የለም ድምጻቸው አይሰማም፡ድምጻቸውም ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ አለም ዳርቻ ወጣ፡፡>>
ሰማየት ቃል የላቸውም ግን በሚገባን ቋንቋ እነሱን የከሸነና የፈጠረ ሀያል አምላክ እንዳለ ይናገራሉ፡፡አልበርት አንስታይን እንዲህ ብሏል፡-<<the more I study science,the more I believe God>> በአማርኛ በቀጥታ ስንተረጉመው፡-<< ብዙ ሳይንስን ባጠናሁ ቁጥር ፣እግዚአብሄርን በጨመረ ሁኔታ እንዳምን ሆኛለሁ>>ብሎ ተናግሯል፡፡በሌላ አገላለጽ ሰማየትን ባየሁና በተመራመርሁ ቁጥር የበለጠ ጌታን እንዳምነው እያደረጉኝ ነው ማለቱ ነው፡ምክንያቱም ሰማየት የእግዚአብሄርን ክብር በሚገባ ሁኔታ እንዲናገሩ ሆነው ስለተፈጠሩ ነው፡

## 2.መጽሀፍ ቅዱስን ገልጠን ስናነብ ይናገረናል

ወደ መጽሀፍ ቅዱስ በትህትና ቀርበን በሰከነ ሁኔታ ብናነበውና ብናጠናው ያስደንቀናል፡፡ምሳሌ 24፡4 <<ላይ በእውቀት ከከበረወና ካማረው ሀብት ጓዳዎች ይሞላሉ>> እንደሚል ጊዜ ሰጥተን መጽሀፍ ቅዱሳችንን ብናጠና በእውቀት እንሞላለን፤ጌታ ወስጡ በታጨቁት ወርቃማ ቃሎቹ ይናገረናል፤አካሄዳችን በሚስተካከል ፍጻሜቻችንን ይቀይራል፡፡የሚያስፈልገን አንድ ነገር ብቻ ነው እንዲናገረን ፈቃደኝነት ነው፡ልባቸንን ከከፈትንና ፈቃደኛ ከሆንን በሚገባ ይናገራል፡፡የእግዚአብሄር ቃል ሲናገረን ደግሞ ወጤት አለው፤ለወጥ ያመጣል፡፡መዝ 19፡7-11 ላይ የእግዚአብሄር ቃል ሲናገረንና ወደ ወስጣችን ሲገባ ያሉትን ለወጦች በሚደንቅ ሁኔታ ዘርዝሯቸዋል፡-

- ነፍስን ይመልሳል(ነፍስን ከጥፋት ያስመልጣል)
- ህጻናትን ጠቢብን ያደርጋል(ብስለት ከፈለጋችሁ ወደ ዚህ ቃል ማምጣት ነወ፤ከምትገምቱት በላይ ይቀይራችኋል)
- አይንን ያበራል(መንፈሳዊው አለም እንድንረዳው ያደርጋል)
- ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል(በምድራዊ ቋንቋ መግለጽ የማይቻል ሀሴትና ደስታ አለው)
- የሰማነውን ቃል ስንጠበቀው በሁሉም የህይወታችን አቅጣጫ ይጠቅመናል

## 3.በመንፈሱ ለልባችን ይናገረናል

እዚህ መዝ 19 ፡12-14 ላይ ዳዊት በጸሎት ቋንቋ የሚገርም መንፈሳዊ ሚስጥርን ይናገራል፡፡ቃሉ እንዲህ ይነበባል፡-
<<ስህተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ሀጢያት አንጻኝ፡፡የድፍረት ሀጢያት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠበቅ፤የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ ከታላቁም ሀጢያት እነጻለሁ፡አቤቱ ረድኤቴ መድህኒቴም የአፌ ቃልና የልቤ ሀሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን፡፡>>እዚህ ቃል ላይ እየተናገረ ያለው መንፈስ ቅዱስ ወስጣችንን እየፈተሸና እየመረመረ በብርሀኑ ካልስታወቀን በስተቀር ብዙ ከእኛ የተሰወሩ ጸያፍ ነገሮች በወስጣችን እንደሚኖሩ ነው፡በዝርዘር ብጠቅሳቸው የተጠቀሱ ሶስት ሀጢያቶች አሉ ፡-

- የተሰወረ ሀጢያት

- የድፍረት ሀጢየት(ታላቁ ሀጢየት)

- ግብዝነትና ሽንገላ(የአፌ ቃልና የልቤ ሀሳብ በፊትህ ያሚ ይሁን የሚለው ይህንን ያሳየናል)

የእግዚአብሄር መንፈስ ካላሳየንና ካልተናገረን ንጹህ የሆንን ሁሉ ማስሎ ልንቀጥል እንችላለን፡፡ነገር ግን በጌታ ፊት ከምር ወድቀን እባክህ በልባችን ተሰወረው ያሉ አንተ የማትወዳቸውን እርሞችን አሳየን ብለን በቅንነት ብንጮሀ በሚባን መንገድ ይናገረናል ያሳየናልም፡እነዚያን እርም የሆኑ ነገሮች ያኔ በማታዘዝ አንቅረን ብንተፋቸው ግንኙነታችንን እና ህብረታችን እየጠለቀ ይመጣል፤እንነጻለን፡፡ብሎም ከሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በጸሎት ብናጠበቅ እና ቃሉን ብናሰላስልና ብናጠና እግዚአብሄርን መፍራት ወደ ህይወታችን ስለሚመጣ የድፍረት ሀጢየቶችን የመተው አቅም እናገኛለን፡፡ከዚህም የተነሳ መንፈሳችን ንቁ (sensitive) ስለሚሆን እርሱን በየትኛው ሜልኩ ማብደል እየከበደንና እየተቀደስን እንመጣለን፡፡
እየሱስ ክርስቶስን አምነን እንደ ግል አዳችን የተቀበልን ሰዎች እግዚአብሄር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በሶስት መንገዶች ይናገረናል፡፡እነሱም -

- በህሊናችን (thru our conscience)

------->የእግዚአብሄር መንፈስ ቀድመን ያነበብናቸውን ቃሎች ወደ ህሊናችን በማምጣት ድርጊቶቻችን እንድናመካከር በማድረግ ይናገረናል፤እንድናስተካክልና በራሱ መንገድም እንድንራመድ ያደርገናል

- በለሆሳስ ድምጽ(subtle small voice)

-------->የእግዚአብሄር መንፈስ በተለያዩ የህይወት ሁኔታዎች ስናልፍ አቅጣጫ ሊሰጠን፣ሊያጽናናን፣ሊያቀናን ወዘተ ከልል ባለች ልብን በምታሳርፍ ድምጹ ለልባችን ይናገረናል

- ጮክ ባለ ድምጽ (authoritative voice of the Holy Spirit)

--------->ማስሚራችን ተንጋዶ፣አልሰማ ብለነው፣እየሄድንበት ያለው መንገድ አደጋ ከሆነና ወይም መንታ በሆነ መንገድ ላይ ሆነን ስንቸገር አንዳንዴ ጮክ ባለ ድምጽ ሊናገረን ይችላል፡፡ይሄኛው ሁልጊዜ የሚሆን ክስተት አይደለም፡
ኢዮብ 33፡14 <<በአንድም በሌላም ይናገራል ሰው ግን አያስተውልም>>ይላል፡፡ይህ ቃል እውነት ነው፡የሰው ፍጥረት በእንቅልፍ ወስጥ ስላለ ነው እንጂ እግዚአብሄር ያልተናገረበት ዘመን የለም፡በዚህ ዘመን ደግሞ አለማችን በፈጠረበት በልጁ በእየሱስ እየተናገረን ነው፡ስለዚህ እባክህ ጌታ ሆይ ጆሮዬን ክፈተው፣አይኔን ግለጠው፣መንፈሴን አንቃው እና ተናገረኝ እንበለው፡እርግጠኛ ነን ልባችን ከተዘጋጀና በሰከነ ሁኔታ በእግሩ ስር ከተቀመጥን በሚባን መንገድ ይናገረናል፡፡
እባክህ ጌታ ሆይ ለእያንዳንዳችን በሚባን መንገድ ለልባችን ተናገረን!

## ቃሉን የማሰላሰል ሀይል

ቃሉን ማሰላሰል ህይወታችንን እንደሚለውጥ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ችግሩ ባልተከፋፈለ ልብ በትጋት እና በጥሩ ዲሲፕሊን ይህንን መርህ መተግበሩ ላይ ነው፡፡፡

ብዙ ሰዎች ስለ እራሳቸውም ሆነ ስለሚሰሩት ስራ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው የሚያስቡት፡፡ቆም ብለው ቃሉን በማሰላሰልና ከህይወታቸው ጋር በማዛመድ እራሳቸውን አያዩም ድርጊቶቻቸውን አይመረምሩም፡፡

ሀዋርያው ጴጥሮስ «ባላጋራችን ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችን ይዞራል»እንደሚለን ካልተጠነቀቅንንና ካልነቃን ሰይጣን አእምሮአችንን በመከፋፈልና ለጌታ እንዳንሰጥ በማድረግ የቃሉ በረከት ወደ ህይወታችን እንዳይመጣ በማድረግ ፍሬ ቢስ ሊያደርገን ይችላል፡፡ከዚህ ሁሉ ችግር የሚያወጣን ለቃሉ ያልተከፋፈለ ልብን መስጠት ነው፡፡

መዝሙር 1፡1-3 ላይ ያለው መርህ ለስኬታችህ ቁልፍ ሲሆን የማሰላሰልን ጥቅም በሚገባ ያሳየናል፡፡ቃሉ እንዲህ ይነበባል፡-

«ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ ፤በሀጢያተኞች መንገድ ያልቆመ፤በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ፡፡ነገር ግን በእግዚአብሄር ህግ ደስ ይለዋል፤ህጉንም በቀንና በሌሊት «ያስባል-he meditates»፡፡እርሱም በውሀ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፤ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤የሚሰራውም ይከናወንለታል፡፡»

ይህ ቃል የእግዚአብሄርን ቃል ማሰብ ወይም ማሰላሰል ያሉትን ሶስት ጥቅሞች ያሳየናል፡-

- በክርስትና ህይወት በሚገባ መተከልና መደላደል
- የማያቋርጥ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት
- መለኮታዊ ስኬት

ቃሉን ማሰላሰል በህይወታችን የጸሎት መንፈስ(spirit of prayer) እንዲኖር ያደርጋል፡፡ባነበብንና ባሰላሰልን ቁጥር ለጸሎት እንገፋፋለን እንዳውም መልካም የሆነ አዙሪት(positive vicious cycle) በህይወታችን ይመጣል፡፡እርሱም እንዲህ ነው፡-

ቃሉን ማንበብ እና ማሰላሰል---------›የጸሎት መንፈስ--------›በጨመረ ሁኔታ ቃሉን ማንበብና ማሰላሰል-----------›የጸሎት መንፈስ መጨመር --------›ማብቂያ የለውም ---------›

ከአራቱ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ የክርስትና ዲሲፒሊኖች አንዱ ቃሉን ማሰላሰል ነው፡-

- ጸሎት
- ጾም
- ቃሉን ማጥናት ማሰላሰል
- ቃሉን በተግባር ማዋል

አብዛኛውን ጊዜ ጸሎትና ቃሉን ማሰላሰል አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፡፡በእንደዚህ አይነት ዲሲፒሊን ስናሳልፍና ስንተጋ መንፈሳዊው አለም እየተገለጠልንና እየበረታን እንመጣለን፡፡አንድ በእንግሊዝኛ ያገኘሁት መርህ አለ፡-

Meditation(ማሰላሰል)-------->Revelation(መረዳትና መገለጥ)----------> application(ቃሉን መተግበር)

በዚህ መርህ አውድ መሰረት ያልተገለጠልንንና ያልተረዳነውን ቃል በተግባር ማዋል እንደማንችል ነው የሚያሳየን፡፡

ሌላው ቃሉን የማሰላሰል ጥቅምን በተመለከተ መዝ 119፡11 ላይ ግሩም ቃል እናገኛለን፡፡እንዲህ ይነበባል፡- «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» በልባችን ውስጥ ቃሉን የምንሰውርበት አንድ ጥሩ መንገድ ቃሉን ማሰላሰል

ነው፡፡በልባችን የተሰወረውና የጠበቅነው ቃል በፈተና ጊዜ ይጠብቀናል፤ከከፉ ነገሮች ሁሉ ያወጣናል፤ብሎም እግዚአብሄርን ከማሳዘንና ከመበደል እንጠበቃለን ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ቃሉን ማሰላሰል የቃሉ ሀይል በህይወታችን እንዲለቀቅ ያደርጋል ስለዚህም የእግዚአብሄር ጸጋ በህይወታችን ይጨምራል፡፡ከዚህም የተነሳ ያለን ተጽእኖ እየሰፋና ለብዙ ሰዎች በረከት እንሆናለን፡፡ስለዚህ ቃሉን ባልተከፋፈለ ልብ ለማጥናት፤ለማሰላሰል እና በህይወታችን ለመተግበር እንነሳ!

ስሜ በቀለ በላቸው(ዶ/ር) ይባላል፡፡የምኖረው በጌትስበርግ ሜሪላንድ አካባቢ ሲሆን ጌታን መጽሀፍ ቅዱስ በማስተማርና በስነ-ጽሁፍ አገለግላለሁ፡፡በጽሁፎቼ ላይ አስተያየት ለመስጠትና ከኔ ጋር መንፈሳዊ ስራን ለመስራት ለምታስቡ በሚቀጥለው አድራሻ ልታገኙኝ ትችላላችሁ፡-

ስልቅ ቁጥር፡-240-507-9148/240-204-0310

ኢ-ሜይል፡-beke_abay@yahoo.com/bekedesa@yahoo.com

ጌታ ህይወታችሁን ይባርክ!